ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

FINOTE DEMOCRACY VOICE OF ETHIOPIAN UNITY

Web site: www.finote.org
Email: efdpu@aol.com

## ለፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዮ ስርጭት
## ወዳጆችና ደጋፊዎች!!

ፍኖተ ዴሞክራሲ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በናንተ ሙሉ ድጋፍና ትብብር “ሕዝብ የማወቅ መብት አለው” የሚለውን መሰረታዊ መርህ ተግባራዊ እንዲሆን የተቻለውን ሁሉ አድርጓል አሁንም እያደረገ ይገኛል። የፍኖተ ዴሞክራሲ የዜና አቅርቦት፣ ወቅታዊና ዋና ዋና በሆኑ የፖለቲካ፥ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ርዕሶች ላይ የሚደረጉ ትችቶች፥ ጥናታዊ ትንተናዎች፥ ቃለ መጠይቆች፥ የተለያዩ ንባባዊ መግለጫዎች፣ ግንዛቤ ሊያዳብሩ የሚችሉ የትግል ተመክሮዎች አይነተኛ መለያዎቹ ናቸው። ይህንንም ገለጻ እንዲሰጥ በተጋበዘበት መድረክ ሁሉ ማብራሪያዎችን ለአድማጮቹ ሰጥቷል። በተናጠል ለተገናኛቸው ግለሰቦች ደግሞ እንደሁኔታው የፍኖተን ራዕይና ተግባር አስተዋውቋል። በደብዳቤ አምዳችን ከአድማጮቻችን የሚቀርቡልን አስተያየቶች የዚሁ ጥረታችን ውጤቶች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም።

መድበላዊ ሥርዓት እንዲገነባ፣ የፖለቲካ አመለካከት እንዲሰፋና ግልጽነት እንዲኖር፣ በተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ሕዝባችን የራሱንም ሆነ የሀገሩን የወደፊት እጣ ለመወሰን እንዲችል ለማድረግ እንደ ፍኖተ ዴሞክራሲ የመሰሉ የሬዲዮ ስርጭቶች በአማራጭነት በመድረኩ በቀጣይነት መኖር ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ቀናኢ ለሆኑ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ግልጽ ነው። የመለስ አገዛዝ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከሕዝባችን ጋር የገባው ቅራኔ እየተባባሰ በመምጣቱ እጅግ አስቸጋሪ፣ አስከፊና አሳፋሪ የመብት ጥሰትና አፈና በሕዝባችን ላይ እያካሄደ ይገኛል። የመጻፍ፣ የመናገር፣ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት በተገድቧል ቁንጽል ቃላት የሚገለጽ ሳይሆን ጨርሶውኑ የሌለ ነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለነዚህ መብቶች ያለምንም ገደብ መከበር እንደማይመሰረት ደግሞ ቢያንስ ያለፉት አሥራ ሰባት አመታት ከምንጊዜውም በበለጠ ግልጽ ያደረጉት ነው።

በመለስ አገዛዝ ሥርአት ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ሕዝቡ እንዲገለገልባቸው ሳይሆን ውስጣዊ ይዞታቸውን እንዳሻ በመተርጎም ለአገዛዙ ማጠናከሪያና ሕዝብን ለማፈን መጠቀሚያ በተደረጉበት ተጠያቂነቱና አገልግሎቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሆነ የዜና ስርጭት ተቋም በቀጣይነት መኖር ጠቃሚነቱን ከሕዝባችን የበለጠ የሚያውቅ የለም። በሀገሩ ስለሚገኘው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ከተለያየ አቅጣጫ ጠንቅቆ ለማወቅ እንዲችል መድረኩ የተመቻቸለት ሕዝብ ከሚቀርቡለት የተለያዩ አማራጮች ፍላጎቱንና ጥቅሙን በምን ዓይነት ለማስጠበቅ የሚያስችለው ውሳኔ ለመውሰድ የሚቸገር አይሆንም። የፍኖተ ዴሞክራሲ ተደማጭነት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መሄድ ለዚህ ሁኔታ በቂ ምስክር ነው። ከዚህ በበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም እናምናለን።

በመሆኑም በመለስ አገዛዝ የሚካሄዱ የሕዝብን መብት የሚጥሱ፣ ሀገርን የሚጎዱ ተግባሮች፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዳይመሰረት የሚያደርጉ ማናቸውንም ሕጎች፣ ደንቦች፣ እንቅስቃሴዎች፣ በዝርዝር በመተንተንና በማቅረብ እናጋልጣለን። በሌሎች መሰል ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች የሚታሰቡ ሀገርንና ሕዝብን የሚጎዱ እንቅስቃሴዎችንም ፈልፍሎና አቀናብሮ ለሕዝብ ማሳወቁንና የመቋቋሚያ መፍትሄዎችንም መጠቆሙን አቅማችን በፈቀደ መጠን እንቀጥልበታለን።

ትግላችን አቤቱታ ለመለስ አገዛዝ ማቅረብና ሩህሩህነቱን መጠበቅ ሳይሆን ከመሰረተው ሥርአት ጋር እንዲወገድ መታገል ነው። የዜጎችን እኩልነት የሚጻረሩ፣ የሀገር ሉዓላዊነትን የሚሸረሽሩ፣ ብሔራዊ ጥቅምን ለባዕድ የሚሸጡ፣ ሀገሪቷ ያላትን እምቅ ሃብት ብዙሃኑ ተቋዳሽ እንዳይሆን መሰናክል የሚፈጥሩ፣ ብሄራዊ መግባባት እንዳይኖርና ክፍፍል እንዲነግስ የሚፈልጉትን ሁሉ የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻል ዘንድ ፍኖተ ዴሞክራሲ ከሕዝብ ጎን በመሆን የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት በጥረት ላይ ይገኛል። ይህ ተሟልቶ ሊገኝ የሚችለው ግን በሀገር ወዳዱ ሙሉ ድጋፍና እርዳታ ብቻ ሳይሆን በፕሮግራሙ መዳበርና መሻሻል እንዲኖር አስተያየት በመስጠትም ጭምር ነው የሚል የጸና እምነት አለን።

በመሆኑም ይህ ስኬታማ ይሆን ዘንድ

በድረ-ገጻችን፦- www.finote.org
በኢሜይላችን፦- efdpu@aol.com

ወይንም በአድራሻችን፦
Finote Democracy
P.O.Box 73337
Washington DC 20056, USA

እርዳታችሁንና አስተያየታችሁን በተጠናከረ መልክ እንድትልኩልን ወገናዊ ጥሪ ዳግም እናቀርባለን።

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

የዝግጅት ኮሚቴ
ታህሳስ 18 ቀን 2001 ዓ.ም.
ጃኑዋሪ 26 ቀን 2009 ዓ.ም